# መምሪያ ለ MY SCHOOL DC



MY SCHOOL DC

The Public School Lottery

MySchoolDC.org

## ለDCPS እና የህዝብ ቻርተር ትምህርት ቤቶች የDC መደበኛ ማመልከቻ

የትምህርት አመት

**2020 - 2021**

MySchoolDC.org/am 202-888-6336 info.myschooldc@dc.gov

# አማራጮችን በምናብዎ ይሳሉ። ትምህርት ቤትዎን ይምረጡ። እዚህ ይጀምሩ።

## የትምህርት ቤትዎን ዝርዝር ይስሩ

ማወቅ ስለሚፈልጓቸው የትምህርት ቤቶች ዝርዝር ለመስራት ይህን ዎርክሺት ይጠቀሙ። ፍለጋዎን በMySchoolDC.org ውስጥ ያለውን School Finder በመጠቀም መጀመር ይችላሉ። እያንዳንዱን ትምህርት ቤት ካጠኑ በኋላ፣ በጣም በሚወዱት ቅደም ተከተል ይዘርዝሯቸው (1ኛ ምርጫ፣ 2ኛ ምርጫ፣ እና ወዘተ)። እርስዎ በ My School DC እስከ 12 ትምህርት ቤቶች ድረስ ማመልከት ይችላሉ፣ እና በጣም በሚወዱት ቅደም ተከተል መዘርዘር አለብዎ።

| የትምህርት ቤት ስም | የትምህርት ቤት ጉብኝት ቀን | ማስታወሻዎች<br>ለእርስዎ እና ለልጅዎ በትምህርት ቤት ውስጥ እጅግ አስፈላጊ ምንድን ነው? የትኞቹ ትምህርት ቤቶች ናቸው ጥሩ ምርጫ? | ደረጃ |
|---|---|---|---|
| *ምሳሌ፣*<br>*School ABC* | *1/9/20* | *ትምህርት ቤቱ በሳይንስ እና ሂሳብ ላይ ያተኩራል፣ ይህም ለልጄ ትክክለኛ ነው፤ ነገር ግን ትምህርት ቤቱ የሚገኘው እኛ ከምንኖ ርበት 3 ማይሎች ርቀት ላይ ነው (የትራንስፖርት አማራጮችን ማጥናት ያስፈልጋል)* | *3* |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |



**ጥያቄዎች? ለማመልከት ድጋፍ ያስፈልግዎታል?**

በቋንቋዎ እርዳታ ለማግኘት የMy School DC Hotline ጋር በ202-888-6336፣ ከሰኞ-አርብ፣ ከ8 ጥዋት-5 ከሰዓት ድረስ ይደውሉ። ወይም ኢሜይል ያድርጉ በinfo.myschooldc@dc.gov።

# የMY SCHOOL DC አጠቃላይ

የMy School DC መደበኛ ሎተሪ በሁሉም ተሳታፊ ትምህርት ቤቶች ያሉ አዲስ ተማሪዎች ምደባን የሚወስን ነጠላ እና የዘፈቀደ ሎተሪ ነው። መጀመሪያ በማመልከት የሚገኝ ጥቅም ባይኖርም፣ አመልካቾች በማመልከቻ የመጨረሻ የጊዜ ገደብ ማመልከት አለባቸው።

**የትምህርት አመት 2020-21 የሎተሪ የመጨረሻ የጊዜ ገደብ፣**
**ፌብሩዋሪ 3፣** 9-12 ክፍሎች | **ማርች 2፣** መዋእለ ህጻናት 3 – 8 ክፍል

## ሶስት አይነት የ My School DC አሉ፣

1. **ይማሩ፣** ለእርስዎ እና ለልጅዎ እጅግ አስፈላጊ የሆነውን ነገር ያሰላስሉ፣ ከነዚያ ፍላጎቶች ተነስተው ዝርዝር ይስሩ፣ እና የትምህርት ቤት አማራጮችዎን ይመርምሩ።
2. **ያመልክቱ፣** የቤተሰብ አካውንት ለመፍጠር ወደ MySchoolDC.org ይሂዱ እና ማመልከቻዎን ይጀምሩ፣ በጣም በወደዷቸው የቅደም ተከተል የትምህርት ቤት ምርጫዎችዎን ደረጃ ይስጡ፣እና ማመልከቻዎን በማመልከቻ የመጨረሻ የጊዜ ገደብ ያስገቡ።
3. **ይመዝገቡ፣** ልጅዎ እንዲመዘገብ አንዴ ግብዣ ከቀረበለት በኋላ፣ የሚያስፈልጉትን ሁሉንም ሰነዶች ያዘጋጁ እና በተገለጸሎት የጊዜ ገደብ ልጅዎን ትምህርት ቤቱ ውስጥ ያስመዝግቡ።

## My School DCማን ያስፈልገዋል?

**የ My School DC ማመልከቻ ያስገቡ የእርስዎ ልጅ አዲስ ተማሪ የሚሆን ከሆነ በ፣**

- በማንኛውም DCPS ትምህርት ቤት፣ (በወሰንዎ ውስጥ ያለውን ትምህርት ቤት ጨምሮ)፣ የመዋእለህጻናት 3 ወይም መዋእለ ህጻናት 4
- ከወሰንዎ ውጭ የDCPS ትምህርት ቤት ወይም  የትምህርት ቤት ቅደም ተከተል (ቅድመ መዋእለ ህጻናት3-ክፍል 12)፣ በመላው ከተማ ባሉ ትምህርት ቤቶች ያሉ DCPS ጨምሮ
- DCPS መራጭ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ወይም ፕሮግራም(ከ9-12 ክፍሎች)
    + ለመረጃ ገጽ 5 ይመልከቱ
- ተሳታፊ የህዝብ ቻርተር ትምህርት ቤት (ቅድመ መዋእለ ህጻናት3-ክፍል 12)

**ምክር፣** ከDistrict of Columbia (ኮሎምቢያ ግዛት) ውጭ የሚኖር እያንዳንዱ ከK–12 ተማሪ የMy School DC ማመልከቻ ማስገባት ሳይኖርበት በቀጥታ ቢያንስ አንድ የDCPS ትምህርት ቤት ውስጥ የመመዝገብ መብት አለው። በወሰንዎ ውስጥ ያለ ትምህርት ቤት ለመፈለግ በMySchoolDC.org ውስጥ ያለውን School Finder ይጠቀሙ።

**My School DC ማመልከቻን ማስገባት <u>አያስፈልግዎትም</u>  ልጅዎ ከሆነ፣**

- አሁን ባለው ትምህርት ቤቱ የሚቆይ ከሆነ (በድጋሚ ለመመዝገብ ትምህርት ቤትዎን ያግኙ)
- የነሱን የDCPS በወሰን ውስጥ ወይም በቅደም ተከተል ባለ ትምህርት ቤት ውስጥ ይማሩ (K-12 ክፍሎች)

My School DC ሎተሪ ማመልከቻ በ ዲሴምበር 16፣ 2019ይጀምራል። ማመልከቻው በእንግሊዘኛ እና በስፓኒሽ ይኖራል። የማመልከቻ መምሪያዎች በአማርኛ፣ ቻይንኛ፣ ቬትናሚዝ፣ እና ፈረንሳይኛ በMySchoolDC.org ውስጥ ለማውረድ ይገኛሉ። በቋንቋዎ እርዳታ ለማግኘት My School DC Hotline ጋር በ (202) 888-6336 ይደውሉ፣ ከሰኞ-አርብ፣ 8ጥዋት - 5 ከሰዓት።



## ይማሩ

**መጀመሪያ፣ ለእርስዎ እና ለልጅዎ እጅግ አስፈላጊ የሆነውን ነገር ያሰላስሉ።**

- ትምህርት ቤቱ የሚገኝበት ስፍራ ምን ያክል አስፈላጊ ነው? ልጄን ወደ ትምህርት ቤት እንዴት አደርሳለሁ?
- የመጀመሪያ እና የመጨረሻ እንክብካቤ ለኔ ቤተሰብ ምን ያክል አስፈላጊ ነው?
- ለልጄ ምን ተመራጭ የመማሪያ ሁኔታ ምን አይነት ነው?
- ለልጄ አስፈላጊ የሆኑ ከመደበኛ ትምህርት ውጭ የሆኑ አቅርቦቶች ምንድን ናቸው?
- ለልጄ ምን አይነት ትምህርት ነክ ያልሆኑ አቅርቦቶች አስፈላጊ ናቸው?

**ፍላጎቶችዎን የሚያሟሉ የህዝብ ትምህርት ቤት አማራጮችን በተመለከተ ይወቁ። የሚከተሉት ጥቂት ጥሩ የጅማሬ ነጥቦች ናቸው፣**

- **MySchoolDC.org ይጎብኙ።**
  - በአቅራቢያዎ ያሉትን DCPS እና የህዝብ ቻርተር ትምህርትቤቶች፣ በወሰንዎ ውስጥ ያሉ የDCPS ትምህርት ቤቶችን ጨምሮ በአድራሻ፣ ክፍል፣ እና በፕሮግራም አይነት **ለመፈለግ School Finder ይጠቀሙ።**
  - ስለ ተሳታፊ ትምህርት ቤቶች እና ክፍት የሆነ የቤት ውስጥ የጊዜ ሰሌዳቸውን **ለማወቅ የMy School DC የትምህርት ቤት አጭር ታሪኮች ይመልከቱ።**
- ስለፕሮግራሞቻቸው ጥያቄዎች ካሉት **ትምህርት ቤቶችን ይጎብኙ ወይም በቀጥታ ትምህርት ቤቶችን ይጎብኙ።** ትምህርት ቤቶችን መጠየቅ ስለሚችሏቸው ጠቃሚ የጥያቄዎች ዝርዝር ከ MySchoolDC.org ማውረድ እና መመልከትዎን ያረጋግጡ!
- እርስዎ የሚፈልጓቸው ትምህርት ቤቶች ውስጥ **የሚማሩ ጎረቤቶችዎ ወይም ጓደኞችዎ ጋር ያውሩ እና ወደ EdFEST** – አመታዊ የህዝብ ትምህርት ቤት ዝግጅት– እና ሌሎች የትምህርት ቤት ዝግጅቶች ጋር ይሂዱ።

**ምክር፣** በገጽ 1 ላይ ያለው ዎርክሺትን በመጠቀም የትምህርት ቤቶችዎን ዝርዝር ይከታተሉ 1!



**ጥያቄዎች? ለማመልከት ድጋፍ ያስፈልግዎታል?**

በቋንቋዎ እርዳታ ለማግኘት የMy School DC Hotline ጋር በ202-888-6336፣ ከሰኞ-አርብ፣ ከ8 ጥዋት-5 ከሰዓት ድረስ ይደውሉ። ወይም ኢሜይል ያድርጉ በinfo.myschooldc@dc.gov።

# ያመልክቱ

## መጀመሪያ፣ የMy School DC የቤተሰብ አካውንት በ MySchoolDC.org ላይ ይፍጠሩ።

- **አንድ የቤተሰብ አካውንት ይፍጠሩ።** ይህን አካውንት ወደ አዲስ ትምህርት ቤት ለሚያመለክት ለእያንዳንዱ ልጅ ማመልከቻ ለማስገባት ይጠቀሙበታል።
- እርስዎ **ኢሜይል አድራሻ** መስጠት እና **የማለፊያ ቃል** መፍጠር ያስፈልግዎታል። የኢሜይል አድራሻ ከሌሎት፣ ከዚያ ይልቅ የተጠቃሚ ስም መፍጠር ይችላሉ።

## ቀጥሎ፣ My School DC ማመልከቻ ይጀምሩ።

**የMy School DC ማመልከቻ ለመሙላት የሚከተሉት መረጃ ያስፈልግዎታል፣**

- **ስለልጅዎ መረጃ**
  - ስም፣ የትውልድ ቀን፣ ያሁን ትምህርት ቤት፣ እና የሚያመለክቱበት ክፍል
  - የእህት ወይም የወንድም መረጃ
- **ስለ ቤተሰብዎ መሰረታዊ መረጃ**
  - የህጋዊ ሞግዚት ስም (የመጀመሪያ እና የአያት ስም)
  - የተጠሪ መረጃ፣ የሞግዚት የቤት አድራሻ ጭምር
- **የትምህርት ቤት ምርጫዎች**
  - እስከ 12 ትምህርት ቤቶች ድረስ መምረጥ ይችላሉ
  - 1ኛ ምርጫዎን (በጣም የሚፈልጉትን ትምህርት ቤት)፣ ከዚያ 2ኛምርጫ፣ እና ወዘተ እያሉ ይዘርዝሩ። ምርጫዎችዎ እርስዎ **በጣም በሚወዱት ቅደም ተከተል** ደረጃ እንደተሰጣቸው ለማረጋገጥ ምርጫዎችዎን በድጋሚ ይመርምሩ።

**ጠቃሚ፣ ትምህርት ቤቶችዎን የሚዘረዝሩበት ቅደም ተከተል አስፈላጊ ነው!** ተማሪዎች ሊዛመዱ የሚችሉት ከአንድ **ትምህርት ቤት ጋር ብቻ ነውእና** ተጠባባቂ የሚሆኑት ከተዛመዱበት ወይም ከተመዘገቡበት ትምህርት ቤት ከፍ ያለ ደረጃ ያለው ትምህርት ቤት ጋር ብቻ ተጠባባቂ ይሆናሉ።

## በመጨረሻ፣ ማመልከቻዎን በመጨረሻ የጊዜ ገደብ ያስገቡ!

- **ፌብሩዋሪ 3፣ 2020፣** ከ9-12 ክፍሎች የማመልከቻ የመጨረሻ የጊዜ ገደብ
- **ማርች 2፣ 2020፣** መዋእለህጻናት 3 – 8 ክፍል የማመልከቻ የጊዜ ገደብ የመጨረሻ ቀን

**ማስታወሻ፣** በማመልከቻዎ ላይ ማንኛውም ማሻሻያዎች ለማድረግ እስከ ጊዜ ገደቡ የመጨረሻ ቀን ድረስ እና ከፈለጉ የትምህርት ቤት ደረጃዎችዎን በድጋሚ ለማዘዝ እስከ ማርች 15 ድረስ ጊዜ አሎት።

# DCPS የተመረጡ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርትቤቶች እና ፕሮግራሞች-የማመልከቻ ፍሬነገሮች እና የመግቢያ ሂደት ለ20-21 የትምህርት አመት

ልጅዎ ለተመረጡ DCPS ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ወይም ፕሮግራም እያመለከተ ነው? እነዚህ ትምህርት ቤቶች በMy School DC ማመልከቻ አማካኝነት የሚሞላ ተጨማሪ የማመልከቻ ክፍሎች። ለበለጠ መረጃ የመጣጥፍ ጥያቄዎችን ጭምር፣ በ**MySchoolDC.org** “ያምልክቱ” የሚለውን ይጎብኙ።

ከእያንዳንዱ ትምህርት ቤት እና ፕሮግራም የመምረጫ መስፈርትን ለማወቅ ከታች ያለውን ቻርት ይመልከቱ።

**ምክር፣** የሎተሪ ማመልከቻ ከመጨረሻ የጊዜ ገደብ **ፌብሩዋሪ 3፣ 2020** በፊት የማመልከቻውን ሁሉንም ክፍሎች ልጅዎ እንዲሞላ ለማስቻል አስቀድመው ያቅዱ።

| ትምህርት ቤት | የማመልከቻ ክፍሎች | | | | የመግቢያ ሂደቶች ** |
|---|---|---|---|---|---|
| | ሪፖርት ካርድ | PARCC ውጤቶች* | መጣጥፍ | ምክረሀሳቦች (በMy School DC ማመልከቻ አማካኝነት ኦንላይን የተሞላ።) | |
| Bard High School Early College DC (ባርድ ሃይ ስኩል ኧርሊ ኮሌጅ ዲሲ) | የመጨረሻ ፈተና የትምህርት አመት 18-19 እና ለ11ኛ ክፍል ተማሪዎች ለየምህርት አመት 19-20 የመጀመሪያ ሩብ አመት ሪፖርት ካርዶች ይጠየቃል። 2.0 GPA ወይም ከዚያ በላይ ይመከራል። | አይደለም | አዎ (Bard (ባርድ) ውስጥ የሚሞላ፣ በMy School DC ማመልከቻ አማካኝነት አይደለም።) | የሂሳብ አስተማሪ፣ | የማመልከቻ ምርመራ፣ መጣጥፍ (በፈተና ቦታ)፣ የግል ቃለመጠይቅ |
| Benjamin Banneker High School (ቤንጃሚን ባነከር ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት) | የትምህርት አመት 19-20 የመጀመሪያ ሩብ አመት | አዎ | አዎ | የእንግሊዘኛ አስተማሪ፣ | የማመልከቻ ምርመራ፣ የቤተሰብ ቃለመጠይቅ |
| Columbia Heights Education Campus (ኮሎምቢያ ሄይትስ የትምህርት ካምፓስ) | የትምህርት አመት 19-20 የመጀመሪያ ሩብ አመት በትምህርት የተገኘበት ጊዜ በሪፖርት ካርዱ ውስጥ መካተት አለበት። | አይደለም | አይደለም*** | የእንግሊዘኛ አስተማሪ፣ የሂሳብ አስተማሪ | የማመልከቻ ምርመራ፣ የግል ቃለመጠይቅ |
| Duke Ellington School of the Arts (ዱክ ኤሊንግተን ስኩል ኦፍ አርትስ) | የትምህርት አመት19-20 የመጀምሪያ ሩብ አመት በሪፖርት ካርዱ የጊዜ መቆጣጠሪያ መካተት አለበት። | አይደለም | አዎ | የሂሳብ አስተማሪ፣ የአርት አስተማሪ (ወይም ሌላ)፣ አማካሪ (ካውንስለር) | የማመልከቻ ምርመራ፣ ፈተና፣ የአካዳሚክ ምደባ ምዘና፣ የቤተሰብ ቃለመጠይቅ |
| Early College Academy (ኧርሊ ኮሌጅ አካዳሚ) @ Coolidge (ኩሊጅ) ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት | የትምህርት አመት 19-20 የመጀመሪያ ሩብ አመት | አዎ | አዎ (በEarly College Academy (ኧርሊ ኮሌጅ አካዳሚ) @ Coolidge (ኩሊጅ) ውስጥ የሚሞላ፣ በMy School DC ማመልከቻ አማካኝነት አይደለም።) | የእንግሊዘኛ አስተማሪ፣ የሂሳብ አስተማሪ፣ | የማመልከቻ ምርመራ፣ መጣጥፍ (በፈተና ቦታ)፣ የቤተሰብ ቃለመጠይቅ |
| McKinley (ሚክንሊ )ቴክኖሎጂ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት) | የመጨረሻ ፈተና የትምህርት አመት 18-19 እና የትምህርት አመት 19-20 የመጀመሪያ ሩብ አመት 3.0 ወይም ከዚያ በላይ GPA እንዲኖር ይመከራል። | አዎ | አዎ(McKinley Tech (ሚክኒሊ ቴክ) ውስጥ የሚሞላ፣ በMy School DC ማመልከቻ አማካኝነት አይደለም።) | የእንግሊዘኛ አስተማሪ፣ የሂሳብ አስተማሪ፣ አማካሪ (ካውንስለር) | የማመልከቻ ምርመራ፣ መጣጥፍ (በፈተና ቦታ)፣ የግል ቃለመጠይቅ |
| Phelps Architecture, Construction, and Engineering High School (ፌልፕስ አርኪቴክቸር፣ ኮንስትራክሽን፣ እና ኢንጂነሪንግ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት) | የትምህርት አመት 19-20 የመጀመሪያ ሩብ አመት በትምህርት የተገኘበት ጊዜ በሪፖርት ካርዱ ውስጥ መካተት አለበት። | አዎ | አዎ | የእንግሊዘኛ አስተማሪ፣ የሂሳብ አስተማሪ | የማመልከቻ ምርመራ፣ የቤተሰብ ቃለመጠይቅ |
| School Without Walls (ስኩልስ ዊዝአውት ዎልስ) ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት | የመጨረሻ ፈተና የትምህርት አመት 18-19 3.0 ወይም ከዚያ በላይ GPA ያስፈልጋል። | አይደለም | አይደለም | አይደለም | የማመልከቻ ምርመራ፣ የመግቢያ ፈተና፣ የተማሪ እና የወላጅ ቃለመጠይቅ |

*ተማሪ PARCC ካልወሰደ፣ ከMy School DC ማመልከቻ ጋር ሌሎች መደበኛ የመንግስት የፈተና ውጤቶችን ለሚጠይቁ ትምህርት ቤቶች እነሱን ያካቱ። **ለማመልከት ምንም አነስተኛ ውጤት አይጠየቅም።**
**ስለ ትምህርት ቤቶች የቅበላ ሂደቶች የበለጠ ዝርዝር ለማግኘት MySchoolDC.org ይመልከቱ።
***አመልካቾች በ My School DC ማመልከቻ የተማሪ ፍላጎት የዳሰሳ ጥናት እንዲሞሉ ይጠየቃሉ።



**ጥያቄዎች? ለማመልከት ድጋፍ ያስፈልግዎታል?**

በቋንቋዎ እርዳታ ለማግኘት የMy School DC Hotline ጋር በ202-888-6336፣ ከሰኞ-አርብ፣ ከ8 ጥዋት-5 ከሰዓት ድረስ ይደውሉ። ወይም ኢሜይል ያድርጉ በinfo.myschooldc@dc.gov።



# መመዝገብ

## የሎተሪ ውጤቶችዎን ሲቀበሉ ምን ማድረግ አለብዎ?

የሎተሪ ውጤቶች በ **ማርች 27፣ 2020** ላይ ይገለጻሉ። የልጅዎን በተጠባባቂ ዝርዝር ላይ አሁን ያለውን  ቦታ በ **MySchoolDC.org** የቤተሰብዎ አካውንት ውስጥ በመግባት ማየት ይችላሉ።

ልጅዎ ከትምህርት ቤት በሎተሪ ከተዛመደ፣ በዚያ ትምህርት ቤት ለመመዝገብ እስከ **ሜይ 1፣ 2020**ጊዜ አሎት። ልጅዎ ከተጠባባቂ ዝርዝር ውስጥ ቦታ ከተሰጠው፣ በትምህርት ቤቱ በተነገርዎት የመጨረሻ የጊዜ ገደብ ውስጥ ማስመዝገብ አለብዎ። በእነዚህ የመጨረሻ የጊዜ ገደቦች የማያስመዘግቡ ቤተሰቦች በትምህርት ቤቱ ውስጥ ቦታቸውን ሊያጡ ይችላሉ።

## ምዝገባ የሚካሄደው ትምህርት ቤት ውስጥ ነው፣ እና ወላጅ ወይም ህጋዊ ሞግዚት በትምህርት ቤቱ ውስጥ ልጃቸውን የማስመዝገብ ሃላፊነት አለባቸው።

**ለመመዝገብ፣ የሚከተሉትን ማድረግ አለብዎ፣**

- **የDC ኗሪ መሆንዎን ማረጋገጥ።** የቤትዎን አድራሻ ለማሳየት ሊጠቀሟቸው የሚችሉ የሰነዶችን ዝርዝር ለማየት ወደ **MySchoolDC.org** ይሂዱ።
- **የትምህርት ቤቱን ተጨማሪ የመመዝገቢያ መስፈርቶችን** ፣ የሚያስፈልገውን ሁሉንም የጤና እና የክትባት ሪከርዶችን ጨምሮ ይከተሉ።
- **የMy School DC የቦታ ተቀባይነት ቅጽ ያስገቡ።** ቅጹን ከ**MySchoolDC.org** ያውርዱ።

**በተዛመዱበቱ ትምህርት ቤት ልጅዎን ማስመዝገብ ልጅዎን ከሌሎች ትምህርት ቤቶች የተጠባባቂ ዝርዝር እንዲሰረዝ አያደርገውም።** የልጅዎ በተጠባባቂ ዝርዝር ላይ አሁን ያለውን ቦታ በማናቸውም ጊዜ በ MySchoolDC.org የቤተሰብዎ አካውንት ውስጥ በመግባት ማየት ይችላሉ። ከተጠባባቂ ዝርዝር ውስጥ ጥሪዎች አስተማማኝ አይደሉም። የሎተሪ ውጤቶችን ለመረዳት እና የተጠባባቂ ዝርዝር እንዴት እንደሚሰራ መረጃ ለማግኘት ወደ MySchoolDC.org ይሂዱ።

# MY SCHOOL DC፣ የህዝብ ትምህርት ቤት ሎተሪ

## ማስታወስ የሚገቡ ቀናቶች

**ዲሴምበር 14፣ 2019** | EdFEST – አመታዊው የህዝብ ትምህርት ቤት ዝግጅት

**ዲሴምበር 16፣ 2019** | My School DC ማመልከቻ ይጀምራል

**ፌብሪዋሪ 3፣ 2020** | ከ9-12 ላሉ ክፍሎች የማመልከቻ የመጨረሻ የጊዜ ገደብ

**ማርች 2, 2020** | ከመዋዕለ ህጻናት3 – 8 ክፍል የማመልከቻ የመጨረሻ የጊዜ ገደብ

**ማርች 27፣ 2020** | የሎተሪ ውጤቶች ይገለጻሉ

**ሜይ 1፣ 2020** | ለተዛመዱ ቤተሰቦች የመመዝገቢያ የመጨረሻ የጊዜ ገደብ

**MySchoolDC.org**

**info.myschooldc@dc.gov**

**202.888.6336**

**@MySchoolDC**

**/MySchoolDC**

**@MySchoolDC**

For assistance in your language, call 202.888.6336.

Para recibir ayuda en su idioma, llame al 202.888.6336.

በቋንቋዎ እርዳታ ለማግኘት፣ ይደውሉ 202.888.6336።

如果需要语言方面的帮助，请拨打 202.888.6336。

Để được hỗ trợ bằng ngôn ngữ của quý vị, hãy gọi 202.888.6336.

Pour obtenir de l’aide dans votre langue, appelez le 202.888.6336.